# ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ
# ዓለም አቀፍ አመራር

# KINIJIT FOR UNITY AND DEMOCRACY PARTY
# INTERNATIONAL LEADERSHIP

## *የሞራል ድርጅታዊና ሀገራዊ ግዴታችንን በጋራ እንወጣ*

*ቅንጅት ለአንድነትና ዲሞክራሲ ፓርቲ ከኢትዮጵያ ህዝብ ያገኘው ተቀባይነት ያመነው ህዝብ፤ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ፤ ለአንድነትና ለፍትህ የሚያደርገውን ትግል የመምራትና የማሳካ ት የሞራል ግዴታ አለበት።*

*የቅንጅት ፓርቲ መሪዎች ለሰላምና ለዲሞክራሲ፤ ለህዝብ መብትና ለፍትህ ሲሉ በኢህአዴግ መንግስት ፤ እንደተራ ወንጀለኛ ተከሰው በእስር ይማቅቃሉ። የነሱ መታሰር የቅንጅት አመራር ክፍተት እንዳይኖረው በማሰብ እስካሁን በተለያየ መንገድ ትግሉ ቀጥሎ ቀይቷል።*

*በዚህ መሰረት፤ በውክልና በሀገር ውስጥ ላለው የቅንጅት አመራር፤ የፖለቲካ ድጋፍ የሚሰጥና የሚያስተባብር፤ እንዲሁም በመላው ዓለም የሚገኘውን የቅንጅት ደጋፊዎች እንቅስቃሴ የሚያቀናጅ የቅንጅት አለም አቀፍ አመራር ቡድን ማቋቋም ጠቃሚ መሆኑን በማመን፤ በእስር ላይ የሚገኙ መሪዎቻችን ቡድኑን በመሰየም መመርያ ሰጥተዋል።*

*ቅንጅት በአሁኑ ጊዜ፤ በሀገር ውስጥ የሚያደርገው ሁለገብ እንቅስቃሴ በየደረጃው የሚወሰኑ ውሳኔዎች፤ የሚካሄዱ ድርድሮችና ስምምነቶች ጠንካራና ግልፅ የፖለቲካ አመራር ሊኖራቸው ይገባል። ይህ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው።*

*በታሰሩት መሪዎቻችን ታምኖበት አዲስ የተሰየመው የቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር ኮሚቴ የተጣለበትን ከባድ ኃላፊነት ለመወጣት መንቀሳቀስ ጀምሯል።*

*ለዚህም በሀገር ውስጥ ትግሉን ለመቀጠልና የታሰሩ መሪዎቻችንን ለማስፈታት የሚያስፈልገውን ሁሉ ለማድረግ የሚከተለውን መልእክት ያስተላልፋል።*

*1. የቅንጅት አመራር መተክያ የሌላቸው በእስር ላይ የሚገኙት መሪዎች ናቸው*

*2. የቅንጅት አመራር  በምንም አይነት ከኢትዮጵያ አይወጣም*

*3. የዓለም አቀፍ አመራሩ፤ የሀገር ውስጥ አመራሩ በኢህአዴግ በሚደረግበት ተጽእኖ የሚኖረውን ክፍተት በመሙላት ድጋፍ ይሰጣል።*

*4. በየአከባቢው የተቋቋሙ የድጋፍ ድርጅቶች በሙሉ ከፓርቲው ጋር የነበራቸው ግኑኝነት በተቀናጀ መልኩ ከተወከለው አመራር ጋር ይቀጥላል።*

*5. ለጊዘው በአውሮፓ፤ በካናዳ፤ በደቡብ አፍሪቃ፤ በአውስትራሊያ፤ በኬንያና ዩጋንዳ የቅንጅት ፓርቲ የፖለቲካ ተጠሪዎች ይዋቀራሉ።*

*6. በሀገር ውስጥ ያለው ሁለገብ አደረጃጀትና እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ይቀጥላል።*

*7. በውጭ ሀገር የቅንጅትንና የኢትዮጵያን ጉዳይ ግልጽና ጠንካራ በሆነ መንገድ ለመከታተል የሚያስችል፤ ዓለም ዓቀፍ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ስልት ተግባራዊ ይሆናል።*

*ስለዚህ፤ ለዚህ ከባድና ፈታኝ ሀላፊነት ፤ መሪዎቻችን ባስቀመጡት የትግል አቅጣጫ ለመሳተፍ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የበኩሉን እንዲያደርግ እንጠይቃለን:: በተለያየ መንገድ ድጋፋችሁን የገለፃችሁ ድርጅቶችና በርካታ ዜጎች ምስጋናችንን እናቀርባለን:: የመሪዎቻችንን ትዕዛዝ ተግባራዊ የማድረግ የሞራል ድርጅታዊና ሀገራዊ ግዴታችንን በጋራ እንድንወጣ፤ ለፓርቲው አባላት፤በየደረጃው ለተቋቋሙ የድጋፍ ድርጅቶች፤ ለመላው የኢትዮጵ ህዝብ ጥሪያችንን እናቀርባለን::*

*ቅንጅት ያነገበው የነፃነት መንፈስ ያሸንፋል!*

***የቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር ኮሚቴ***
***ዋሽንግተን ዲሲ***
***ግንቦት 18 1998ዓ.ም.***